# ምዕራፍ ስድስት

# ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ

በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ክርስቲያኖች ያገኙት ጸጋ እጅግ በጣም ብዙ ነው ጥቂቶቹን ከዚህ በታች እንመለከታለን።

## 1. በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ሆንን፤

ይህን በተመለከተ ቅ/ጳውሎስ "በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና" ይለናል (ገላ 3፥26) በኤፌሶን መልእክቱ ደግሞ "በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን።" ይለናል (ኤፌ 1፥5) ሐዋርያው ቅ/ዮሐንስ ደግሞ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" (ዮሐ 1፥12-13) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው በስሙ ሕይወት መድኃኒት እንደሚበዛላቸው አምነው ለተቀበሉት የልጅነት ሥልጣን እንደሚሰጣቸው ነው የሚገልጽልን። ይህም ልጅነት በፍቅረ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ መሆኑን "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ እንዲሁም ነን፤ ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም" በማለት ያብራራልናል (1ዮሐ 3፥1)



አዎን እኛ ክርስቲያኖች ከሰማያዊው አባት ከማይጠፋው ዘር የተወለድን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ስሙ ሕይወት መድኃኒት መሆኑን በመቀበል ነው።

## 2. የልጅነት መንፈስ (የመንፈስ ልደት) ተሰጠን፤

ይህንንም በተመለከተ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" በማለት ገልጾልናል (ሮሜ 8፥14-16) በገላትያ መልእክቱም "ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።" በማለት አክሎበታል (ገላ 4፥6)።

አዎን ከእግዚአብሔር የተወለድን እኛ ክርስቲያኖች የልጅነት መንፈስ ስለተሰጠን በፍጹም እምነት ሳንፈራ አባ አባት ብለን እግዚአብሔርን ልንጠራው ይገባናል። "እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።" (2ጢሞ 1፥7) ተብሎ እንደተጻፈ በእኛ ውስጥ ያለው መንፈስ የፍርሃት አይደለምና።

ክርስቲያን ወገኔ ሆይ ልጅ ከሆንክ የሚከተሉትን መብቶችንና ግዴታዎችን አትዘንጋ።

## 2.1 ልጅ ከሆንክ ወራሽ ነህና ደስ ይበልህ፤

ይህንንም እውነት የእግዚአብሔር ቃል “ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን” (ሮሜ 8÷17) በማለት ይገልጸዋል። እንዲሁም “ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።” በማለት ያጠናክረዋል (ገላ4÷7) አዎን በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ክርስቲያን “ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ” (ማቴ 25÷34) ተብሎ እንደተጻፈ የማይለወጠውን የማይሻረውን የአባቱን ዘለዓለማዊ መንግሥት ይወርሳል። አንተስ ክርስቶስን በማመን ከውኃና ከመንፈስ ተወልደሃልን? የመንግሥቱ ወራሽስ ነህን?

## 2.2 ልጅ ከሆንህ አባ አባት በማለት ለጸሎት የሚያስፈልግህን ከአባትህ ጠይቅ፤

“እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን ከክፉም አድነን እንጂ ወደፈተና አታግባን መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን።” (ማቴ 6÷9-13) በማለት ወደ አባትህ ዘወትር ጸልይ ሰማያዊ አባትህ ምድራዊ አባትህ ከሚያስብልህ ይልቅ አብልጦ ያስብልሃልና “ወይስ ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን



ይሰጣቸው?” (ማቴ 7÷9-11, ሉቃ 11÷15) እንዲሁም “እስከአሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ” ተብሎ ተጽፎአልና ስለሚያስፈልግህ ሁሉ ወደአባትህ ጸልይ። (ዮሐ 16፤24)

## 2.3 ልጅ ከሆንክ አባትህ ሲቀጣህ ታገስ፤

“ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቅልል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፣ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል፤ ለመቀጣት ታገሱ፣ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፦ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፣ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል፣ ለጥቅማችን ይቀጣናል ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።” (ዕብ 12÷6-11, ራዕይ 3÷19, ምሳሌ 3÷11, ኢዮብ 5÷17, ኤር 30÷11, 10÷24) ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር የሚቀጣ የሚወዳቸውን ልጆቹን ነውና የማይቀጣ ግን ዲቃላ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለምና ታገስ።

## 2.4 የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመራ፤

“በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።” ይለናል የእግዚአብሔር ቃል (ሮሜ 8÷14) በእግዚአብሔር ቃል ሰዎችን ሁሉ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ “ግን

እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል" (ዮሐ 16፥13) ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር መንፈስ ነውና።

ክርስቲያን ወገኔ ሆይ አንተ የምትመራው በማን መንፈስ ነው? በእግዚአብሔር መንፈስ ነውን ወይስ በስሜትህ? በል ለሁሉም ከዳዊት ጋር "አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ" በማለት እንጸልይ (መዝ 142፥10) መንገዳችን በጽድቅ መንገድ ይሆንልን ዘንድ።

## 2.5 *የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ አባትህን ምሰል፤*

አባቱን የማይመስል ልጅ ልጅነቱ ያጠራጥራል የእግዚአብሔር ቃል "ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።" (1ጢሞ 4፥7) ይለናል። እግዚአብሔርን መምሰልም ታላቅ ነገር መሆኑን "እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ . . . በክብር ያረገ" ተብሎ ተጽፏል (1ጢሞ 3፥16) በምን በምን እንምሰለው ብንል በቅድስና (1ጴጥ 1፥15)፣ በፍጹምነት (ማቴ 5፥48)፣ በይቅርታ (ሉቃ 6፥36, ኤፌ 4፥32, ቆላ 3፥13)፣ በእነዚህና በሌሎችም አባታችንን ልንመስለው ይገባል።

## 2.6 *የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ባሪያ አትሁን፤*

በክርስቶስ የሚያምን ከእግዚአብሔር የተወለደ ክርስቲያን በክርስቶስ ነጻ ስለወጣ ማንም ሊገዛው አይችልም አይገባምም ይህንን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል "በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶናልና።" (ሮሜ 8፥2)



እንዲሁም "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" ይለናልና (ገላ 5፥1) እንግዲያስ አንባቢ ሆይ በክርስቶስ ያገኘኸውን ነጻነት ትተህ ባሪያ አትሁን።

### *ሀ. የኃጢአት ባሪያ አትሁን፤*

የእግዚአብሔር ቃል "እውነት እውነት እላችኋለሁ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።" ይላል (ዮሐ 8፥34) ነገር ግን ስለእውነተኛ ክርስቲያን "ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።" (ሮሜ 6፥13) "ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና" ይላል (ሮሜ 6፥14) በተጨማሪ አንድ ሰው ለተሸነፈበት ወይንም ድል ለተነሣበት ባሪያ እንዲሆን ማለትም ለኃጢአት ብንሸነፍ ለስካር፣ ለዝሙት፣ ለጣዖት . . . ከተሸነፍን የዚያ ድል የነሣን ባሪያዎች እንደምንሆን "በመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።" (ሮሜ 6፥16) "ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው- አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና" በማለት ያብራራልናል (2ጴጥ 2፥9) አንተንስ ማን ድል ነስቶሃል የማንስ አሽከር ወይንም ባሪያ ሆነሃል?

### *ለ. የነፍስ ገዳዩ የዲያብሎስ አሽከር አትሁን፤*

"እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል

ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።" (ዮሐ 8፥44) "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ" ተብሎ ተጽፎአልና (ያዕ 4፥7) ከዲያብሎስ ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት አይኑርህ።

## ሐ. ባለማወቅ ጣዖታትን በማምለክ የጣዖት ባሪያ አትሁን፤

"ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ።" (ገላ 4፥8) ተብሏልና።

## መ. በክርስቶስ ያለህን አርነት ሊያሳጡህ ለሚሹለከለኩ የሐሰት መምህራን ቦታ አትስጥ፤

"ነገር ግን ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለገቡ ስለሐሰተኞች ወንድሞች፤ ነበረ፤ የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም።" (ገላ 2፥4-5) እንግዲያውስ "በዋጋ ተገዝታችኋል የሰው ባሪያዎች አትሁኑ።" (1ቆሮ 7፥23) ተብሎ እንደተጻፈ በዋጋ ተገዝተናልና የሰው ባሪያ አንሁን ነገር ግን ስለወንጌል ብቻ ራሳችንን ባሪያ ልናደርግ ይገባናል (1ቆሮ 9፥19-23) እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት ለመስበክ (2ቆሮ 4፥5-6) እንዲሁም ስለጌታ ክብር ለሰዎች በመታዘዝ ብቻ ራሳችንን እንድናስገዛ ተመክረናል (1ጴጥ 2፥14-17) ከዚህ ውጪ ማንም ሊገዛን ስለምንም ራሳችንን ባሪያ ልናደርግ አይገባም።

## 2.7 በክርስቶስ ከአሸናፊዎች በለጥን፤

"በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።" ተብሎ ተጽፎአልና (ሮሜ 8፥37)



### 2.7.1 በክርስቶስ ላለን ኩነኔ የለብንም፤

"እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም" (ሮሜ 8፥1)

### 2.7.2 በክርስቶስ ኢየሱስ ሁልጊዜ ደስተኞች እንሆናለን።

"ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ" (ፊልጵ 4፥4) ተብሎ የተጻፈው ይህንኑ ነው የሚያንጸባርቀው።

## 2.8 ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች፤

ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ያለው ፍቅር ታላቅ ነው። በመሆኑም፤

### 2.8.1 ነፍሱን እስከመስጠት ወደደን፤

"እርሱ ስለእኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል" (1ዮሐ 3፥16) "መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል" (ዮሐ 10፥11) ተብሎ እንደተጻፈ እስከሞት ድረስ ነው የሚወደን "ፍቅር እንደሞት የበረታች ናትና" (መኃል 8፥6) ይህ እንደሞት የጸና ከሞትም የጸና መለኮታዊ ፍቅርም ወደር የለሽ ፍቅር ነው። ሐዋርያው የመዘገበልን መለኮታዊ ቃልም የሚያንጸባርቀው ይህንኑ ነው። "ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ተብሎ ተጽፎአልና (ዮሐ 15፥3) አዎን ክርስቶስ ለእኛ ካለው ፍቅር የበለጠ ፍቅር ለማንም የለውም።

### 2.8.2 እስከመጨረሻው ወደደን፤

"የወደዳቸውን እስከመጨረሻው ወደዳቸው" (ዮሐ 13፥1) ተብሎ እንደተጻፈ የወደዳቸውን ሐዋርያት እስከመጨረሻው እንደወደዳቸው እኛን ክርስቲያኖችንም እስከመጨረሻው ይወደናል።

### 2.8.3 ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር ጥልቅ ወደርም የሌለው ስለሆነ ፍቅሩን ለማወቅ እንበርታ፤

"የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ" (ኤፌ 3፥18-19) አዎን የክርስቶስ ፍቅር ጥልቅ ነው።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ ምን አገኙ?
2. የእግዚአብሔር ልጆች ከሆን ምን ማድረግ አለብን?
3. ከአባታችን የምንወርሰው ምንድን ነው?
4. የእግዚአብሔር ልጅነት መለያዎቻችን ምን ምን ናቸው?
5. ክርስቶስ ምዕመናንን የወደደበትን ፍቅር የሚገልጡ ሦስት ነጥቦችን ጥቀስ?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.